ኤፕረል 2018 QuickNotes ቁ. 2

**የፎረስት ኖልስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Forest Knolls Elementary School) አስተማሪ የ MCPS የዓመቱ መምህርት በመሆን ተሰየመች።**

በፎረስት ኖልስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Forest Knolls Elementary School) የሙዓለ ህፃናት መምህርት Kristen Kane የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ 2018 - 2019 የዓመቱ መምህርት በመሆን በ16ኛው ዓመታዊ የትምህርት ልቀት ያላቸውን ለማክበር በተዘጋጀ ክብረበዓል ላይ ተሰይማለች።

Kane በፎረስት ኖልስ (Forest Knolls) ከ2011 ጀምሮ የሙዓለ ህጻናት እና የአንደኛ ክፍል መምህርት ናት። በተጨማሪም የሙዓለ ህፃናት የቡድን መሪ እና የሰራተኞች/staff እና የPTA(የወላጅ መምህር ህብረት) አገናኝ/liaison ናት።

ከዚህ በመቀጠል በሜሪላንድ ስቴት ደረጃ የዓመቱ መምህርት ለመሆን የምትወዳደረው Kane፣ ተባባሪ፣ ታጋሽ፣ እና ሃሳቧን የምታካፍል መምህርት ናት። ከተማሪዎቿ ጋር መልካም ጠንካራ ግንኙነት በመገንባት አዎንታዊ የመማሪያ ክፍል ድባብ በመፍጠር ተማሪዎችን የሚያሳትፋቸው ትምህርት ታቀርባለች። እርሷ የምታስተምርበት ክፍል ደስታ የሰፈነበት፣ ሞቅ ያለ እና አሳታፊ ነው። የተማሪ ምርጫን ለማበረታታት ትምህርትን ለይታ የምትቀርጽ እና የተለያዩ ተማሪዎችዋን ፍላጎቶች የሚያሟሉ ትምህርቶችን ትሰጣለች። ልዩ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የመማር ስንክልና፣ የንግግር እና የቋንቋ ዘገምተኝነት እና የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሆነው በእንግሊዝኛ የሚማሩትን ጨምሮ አብሮ የመሥራት ጥሩ ችሎታ አላት።

ለማጠቃለያ ውድድር ከደረሱት ሦስት መምህራን Kane አንዷ ስትሆን፣ ከእነ Edwina Kollo በሼዲ ግሮቭ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Shady Grove Middle School) የሂሳብ ትምህርት-ይዘት ስፔሻሊስት፣ እና Janet Gallagher በቤተዝዳ - ቼቪቼዝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Bethesda-Chevy Chase High School) የሪሶርስ አስተማሪ ጋር። በማጠቃለያ ለቀረቡት ስያሜ የተሰጠው በ"ማሪያን ግሪንብላት የትምህርት ፈንድ/Marian Greenblatt Education Fund" ነው።

በርካታ ሌሎች የ MCPS ሠራተኞችና የማህበረሰብ አባላትም ላበረከቱት የላቀ አስተዋጽኦ እና ቁርጠኝነት በጀርመንታወን ብላክሮክ የስነጥበብ ማዕከል (BlackRock Center) በተካሄደዉ ለልጆች ሻምፒዮና (Champions for Children) ዝግጅት አስተዋጽኦ እውቅና ተሰጥቷቸዋል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ኤርን ክሮውሊ/Erin Crowley**፣ በሰመርሰት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Somerset Elementary School) የሙዓለ ህፃናት መምህርት፣ የግሪንብላት/Greenblatt የዓመቱ አንፀባራቂ ኮከብ መምህርት፣
- **Helene McLaughlin**፣ በኖርዝውድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Northwood High School) የፊዚክስ መምህርት፣ የግሪንብላት የዓመቱ አንፀባራቂ ኮከብ መምህርት (Greenblatt Rising Star Teacher of the Year)፣
- **Myriam Yarbrough**፣የፔይንት ብራንች ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Paint Branch High School) ርእሰ መምህርት፣ በትምህርት ልቀት የ Dr. Edward Shirley ሽልማት፣
- **Stephen Ricketts**፣ በ ሃሊይ ወልስ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Hallie Wells Middle School) የህንፃዎች ጥገና/እድሳት ማናጀር፣ የዓመቱ የድጋፍ አገልግሎቶች የዓመቱ ምርጥ ሠራተኛ፣
- **Wells Fargo** የቢዝነስ ሻምፒዮና ለልጆች፤ እና
- **Gillian Huebner** የትምህርት ቤት አካባቢና ደህንነት ንዑስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ የPTAs ካውንስል፣ ለልጆች የበጎ ፈቃድ ሻምፒዮና

ዝግጅቱን ለማካሄድ የተቻለው 2018-2019 የዓመቱ ምርጥ መምህር ሽልማት ስፖንሰር ያደረጉ Fitzgerald Auto Mall ን ጨምሮ ከአጋሮች በተገኘ ድጋፍ ነው። ለዓመቱ የምርጥ መምህር አጠቃላይ ውድድር የቀረቡት ሁሉም ተወዳዳሪዎች ከግሪንብላት የትምህርት ፈንድ (Greenblatt Educational Fund) $2,000 (ሁለት ሺህ ዶላር) ሽልማት አግኝተዋል። Kane የ MCPS የዓመቱ ምርጥ መምህርት በመሆኗ ለአንድ ዓመት የመኪና ሊዝ ከ Fitzgerald ታገኛለች።

**ሠላማዊ የት/ቤት ጉዞ ክንዋኔ እስከ ሜይ ተግባራዊነቱ ይቀጥላል።**

*ዓመቱን በሙሉ የሞንጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ መምሪያ* (MCPD) *ባልደረቦች፣ እለት ተእለት ከሚያደርጉት ስለትራፊክ እንቅስቃሴ መቃኘት እና ማህበረሰብን በማስተማር ህግን ከማስከበር ሥራ በተጨማሪ፣ የትራፊክ ደህንነትን የማስጠበቅ ተግባር ላይ ያተኩራሉ። በኤፕሪል፣ የተዘናጋ ማሽከርከርን ለማስቀረት የማስገንዘቢያ ወር፣ በእጅ ስልክ እያወሩ የማሽከርከር ህገወጥነትን ለመከላከል ህግ ለማስፈጸም ትኩረት ሰጥተውበት ይሠራሉ። ሜይ ላይ የፖሊስ መምሪያ የመቀመጫ ቀበቶዎችን እና ለህፃናት አስተማማኝ የመኪና መቀመጫ አገር አቀፍ የአውራ ጎዳና ትራፊክ ደህንነት አስተዳደርን* "Click It or Ticket Campaign" *ግንዛቤ የሚሰጥበት ዘመቻ ላይ ይሳተፋሉ።*

*የሞንጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ -ወደ ት/ቤት በሰላም የመጓዝ ክንዋኔ/*MCPD – Operation Safe Ride To School *ተነሣሽነት በሞባይል ስልክ ተጠምዶ በመዘናጋት ማሽከርከር አደገኛ መሆኑን፣ እና የመኪና መቀመጫ ቀበቶ ስለማሰር እና በመኪና ውስጥ ስለ ህፃናት መቀመጫ አጠቃቀም በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ መግቢያ በሮች እና የት/ቤት ተማሪዎችን ከመኪና ማውረጃ መስመሮች ላይ ጠዋት ላይ ትምህርታዊ እና ህግ የማስከበር ትኩረት ለመስጠት ነው። በዚህ ወር የተጀመረ ሲሆን በሜይ ወርም ይቀጥላል። አሽከርካሪዎች ተማሪዎችን ት/ቤት በሚያወርዷቸው ወቅት መኪና እየነዱ ሞባይል ስልክ እንደሚያወሩ እና ህፃናትን ለአደጋ በማይጋለጡበት ሁኔታ በመኪና መቀመጫ ላይ በትክክል እንደማያስቀምጧቸው በርካታ ቅሬታዎች ወደ መምሪያው ደርሰዋል። ተማሪዎች ወደ ት/ቤት የሚደርሱበት ሠዓት ከፍተኛ የእግረኞችና የተሽከርካሪዎች ትራፊክ የሚጨናነቅበት ወቅት መሆኑን መምሪያው ይገነዘባል። በዚህ ወቅት ሠላምና ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጠው ትኩረት ነው።*

**የአእምሮ ጤንነትና ደህንነት መድረክ ኤፕሪል 22 ይካሄዳል**

እሁድ ኤፕሪል 22፣ ከ1–5 p.m በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Gaithersburg High School) በሚካሄደው ስለ አእምሮ ጤንነትና ደህንነት የውይይት መድረክ ላይ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል።

በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና በሞንጎመሪ ካውንቲ የPTAs ካውንስል (MCCPTA) ትብብር የሚካሄደው ይህ ዝግጅት ዛሬ ወጣቶች ስለሚያጋጥማቸው የአእምሮ ጤንነት ተግዳሮት ላይ መወያየት እና በ MCPS እና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ዉስጥ ያሉት መርጃዎች/ሪሶርሶች ይቀርባሉ።

የእለቱ ክንውን በሞንጎመሪ ካውንቲ የወጣቶች የአእምሮ ጤንነት እና ደህንነት ሁኔታ ውይይትን ያካትታል። ክፍለ ጊዜውን የሚመሩት Ann Mazur, CEO of EveryMind፣ እና በ Richard Montgomery ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጁንየር ተማሪ ለ 2018–2019 የ MCPS የተማሪ ተወካይ ለመሆን እጩ የሆኑት Ananya Tadikonda ናቸው።

ስለ አስቸጋሪ ሁኔታ/ቀውስ ሲፈጠር እንዴት መቋቋም እንደሚቻል እና ራስ መግደልን ስለመከላከል በ Dr. Elizabeth Rathbone፣ የ MCPS የተማሪዎች የጤንነት እና ደህንነት አስተባባሪ፣ እና Rachel Larkin፣ የ EveryMind የአስቸጋሪ ሁኔታ/ቀውስ መከላከያ እና ጣልቃገብነት ዳይሬክተር የሚቀርብ ክፍለጊዜ ይኖራል።

በተነጣጠሉ የጋራ/የቡድን ውይይቶች ላይ፡- ከልክ በላይ ጭንቀት፣ በውጥረት የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን መቆጣጠር፣ የአእምሮ ጥንቃቄ/አስተዋይነት፣ የሚያድሱ እርምጃዎች፣ በማህበራዊ ድረገጾች የልጆችን ደህንነት መጠበቅ፣ የአካል እንቅስቃሴና የአእምሮ ጤንነት፣ እና የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነትን የሚመለከቱ ርእሶች ይዳሰሳሉ። በስፓንሽ ቋንቋ የሚካሄድ በ Identity የሚመራ ውይይትም ይኖራል።/Spanish-language panel led by Identity.

[እዚህ ](#)ይመዝገቡ።

[ስለ አእምሮ ጤንነትና ደህንነት የውይይት መድረክ በራሪ ጽሑፍ](#)

**ለስራ ዝግጁነት የሰመር ካምፖች ምዝገባ ክፍት እየተካሄደ ነው**

በሮቦቲክስ (robotics)፣ በምህንድስና (engineering)፣ ወይም በምግብ አዘገጃጀት ጥበብ (culinary arts) ፍላጎት ያለው/ያላት የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ አለዎት-አለችዎት? የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ስለ ዲስትሪክቱ የሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞች ለማወቅ/ለመማር እንዲችሉ MCPS ተከታታይ የሰመር ካምፖችን እያዘጋጀ ነው።

ተማሪዎች በባልትና ኪነጥበቦች ፕሮግራም ጣፋጭ የሆነ ነገር ማብሰል ይችላሉ ወይም በአውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም እጆቻቸውን ማቆሸሽ ይችላሉ። ቅድመ-ኤንጂኒሪንግ፣ የግጥሚያ ንድፍ እና ከዚያም በላይ መዳሰስ ይችላሉ።

የመጀመርያ ክፍለ ጊዜ ከጁን 25-28 ይካሄዳል። ሁለተኛው ክፍለጊዜ ከጁላይ 9 - 12 ይካሄዳል። ካምፖቹ የሚካሄዱት በጌትስበርግ (Gaithersburg) እና በ ፔይንት ብራንች (Paint Branch) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው። እያንዳንዱ ካምፕ ሁለት የጥናት ፕሮግራሞችን ያካትታል የእያንዳንዱ ካምፕ ተሳትፎ ዋጋ $50 ነው። FARMS ለሚቀበሉ ተማሪዎች የፋይናንስ እርዳታ አለ።

[Career Readiness Summer Camps](#)

**JED በተሰኘው ፖሊሲ ላይ የትምህርት ቦርድ የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥበት ይፈልጋል።**

ኤፕሪል 12/2018 የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ JED የተሰኘውን ክለሳ የተደረገበትን ፖሊሲ በጊዜያዊነት አጽድቋል። ክለሳ የተደረገው ስለ ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና

የትምህርት ምዝገባ/ምደባ፥ እና የፖሊሲውን የመረጃ ጠቋሚ ስያሜ ወደ Policy JEA እንደገና መቀየር በሚለው ላይ ነው።

የክለሣው አስተያየት የሚያረጋግጠው መስፈርት ለሚያሟሉ ለሁሉም የሞንጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች ፍቱን (effective)፣ ቀልጣፋ (efficient)፣ እና መድሎ የሌለበት (equitable) የምዝገባና የምደባ ሒደትን ትግበራ ለማረጋገጥ እና በሜሪላንድ ህግ መሠረት ለነዋሪዎች እና ነዋሪ ላልሆኑ ተማሪዎች የምዝገባ-የምደባ መስፈርቶችን መልክ ለማስያዝ ነው። በጊዜያዊነት የፀደቀው (Policy JED) ረቂቅ ፖሊሲ እስከ ዓርብ ጁላይ 6/2018 ለህዝብ አስተያየት ክፍት ይሆናል። ክለሳ በተደረበት Policy JED ላይ እዚህ ጋ አስተያየት ለመስጠት ይችላሉ።
MGT America ከ MCPS የእድገት ማኔጅመንት እቅድ ጋር የተያያዘ የአማካሪ ሪፖርት። በፖሊሲው ላይ የተደረጉት ለውጦች የሚያተኩሩት ቁልፍ ጉዳዮች ስለምዘና-ግምገማ ሂደት፣ አጠቃላይ የፋሲሊቲዎችን እቅድ ሂደት፣ እና የካፒታል ባጀት በሚታቀድበት ሂደት በየደረጃው የማህበረሰቡን አስተዋጽኦ ማካተት ናቸው።